ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

የሚከተሉትን ጨምሮ በ**ሁሉም** የKing County Sheriff ጽህፈት ቤት (King County Sheriff's Office, KCSO) **ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች** የቋንቋ እርዳታ ይገኛል፡-

- **የአደጋ ጊዜ እና የህዝብ ደህንነት አገልግሎቶች፡-** 911 ግንኙነቶች፣ ምርመራዎች፣ የአደጋ ሪፖርቶች፣ በበይነ መረብ ሪፖርት ማድረግ
- **ፈቃድ መስጠት እና መዝገቦች፡-** የተደበቁ ሽጉጥ ፈቃዶች፣ ከጦር መሳሪያ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች፣ የመዝገብ ጥያቄዎች፣ የማጽዳት ደብዳቤዎች
- **የሕግ እና የፍርድ ቤት አገልግሎቶች፡-** የጥበቃ ትዕዛዞች፣ ማባረሮች፣ የፍትሐ ብሔር ፍርድ ማዘዣዎች፣ ህጋዊ ሰነዶችን ማገልገል
- **የማህበረሰብ እና የድጋፍ አገልግሎቶች፡-** የፆታዊ ጥቃት ወንጀለኛ ምዝገባ እና ፍለጋ፣ የቴራፒዩቲክ ምላሽ ክፍል፣ የU and T ቪዛ ማረጋገጫዎች

ስልክ ቁጥሮች እንደየ ፕሮግራም ወይም አገልግሎት ይለያያሉ። ሊያገኙት የሚሞክሩትን ፕሮግራም አድራሻ መረጃ ለማግኘት ድረ-ገጻችንን እንዲጎበኙ እንመክራለን።

ስለ ሁሉም የKCSO ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በሚከለው ላይ የበለጠ ይወቁ፡-
kingcounty.gov/services

በማህበረሰብዎ ውስጥ የ KCSO የፖሊስ አገልግሎቶች!

Precinct 2
801 228th Ave SE, Suite 202
Sammamish, WA 98075
206-263-9133

Precinct 3
22300 SE 231st St.
Maple Valley, WA 98038
206-477-6446

Precinct 4
14905 6th Ave SW
Burien, WA 98166
206-477-2200

KCSO በ Beaux Arts፣ Burien፣ Carnation፣ Covington፣ Kenmore፣ King County Int'l Airport፣ City of Maple Valley፣ Metro Transit፣ Muckleshoot፣ Newcastle፣ North Bend፣ Sammamish፣ SeaTac፣ Shoreline፣ Sound Transit፣ Skykomish እና Woodinville ጨምሮ **ባልተመዘገቡ የKing County አካባቢዎች** እና **በርካታ የኮንትራት ከተሞችን እና ኤጀንሲዎች** ያገለግላል።

ድንገተኛ አደጋ እና ሪፖርት ማድረግ

- **ለድንገተኛ አደጋዎች፡- ወደ 911 ይደውሉ** በቀን 24 ሰዓታት ክፍት ነው። አስተርጓሚ እንደሚያስፈልግዎ ለላኪው ይንገሩ።
- **ድንገተኛ ላልሆኑ ሁኔታዎች፡- 206-296-3311**
- **በበይነ መረብ ሪፖርት ለማድረግ፡- kingcounty.gov/sheriff**

King County

SHERIFF
KING COUNTY

የቋንቋ መዳረሻ

እርስዎ ስለሚገኙ የቋንቋ አገልግሎቶች ይወቁ!

ይህ ብሮሹር በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።

文A

ትርጉሞችን ለማየት QR ኮድ ስካን ያድርጉ።

KCSO E-187 (5/26) Amh

የቋንቋ መዳረሻ የማግኘት መብትዎ

King County Sheriff's Office (KCSO) በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች አገልግሎቶቻችንን ማግኘት እንዲችሉ የቋንቋ እርዳታ ይሰጣል። እንግሊዝኛ ለመናገር፣ ለማንበብ፣ ለመጻፍ ወይም ለመረዳት ከተቸገሩ ነፃ **የቋንቋ እርዳታ የማግኘት መብት አልዎት።**

የቋንቋ እርዳታ የሚሰጠው **በ1964 የሲቪል መብቶች ህግ ርዕስ VI (Title VI of the Civil Rights Act of 1964)**ን በማክበር ሲሆን ሁሉም የማህበረሰባችን አባላት ከKCSO ጋር በብቃት መገናኘት እንዲችሉ ይረዳል።

የቋንቋ መዳረሻ የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳል። ደህንነት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው።

የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ማንኛውም ሰው አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላል።

King County Sheriff's Office (KCSO) ምን ዓይነት የቋንቋ አገልግሎት ይሰጣል?

- **የጽሑፍ ትርጉሞች**፦ ደብዳቤዎችን፣ ማሳወቂያዎችን፣ ቅጾችን እና መመሪያዎችን ጨምሮ

- **የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**፦ በቪዲዮ፣ በስልክ ወይም በአካል

- **ብቃት ያላቸው ሁለት ቋንቋ የሚናገሩ ተወካዮች እና ሰራተኞች፣** በአንዳንድ ቋንቋዎች ላይ ይገኛሉ

የKCSO አባላት ከእርስዎ ጋር ሲገናኙ የቋንቋ እርዳታ ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቃሉ፤ እርስዎም በማንኛውም ጊዜ ሊጠይቁት ይችላሉ።

በKCSO የቋንቋ አገልግሎቶች ላይ ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን በ kcsolanguageaccess@kingcounty.gov ያግኙን።

በተለይ በሚከተሉት ጊዚያት ላይ የቋንቋ ድጋፍ በጣም አስፈላጊ ነው፦

- በተወካዮች/መኮንኖች ቃለ መጠይቅ ሲደረግ
- መብቶትን ማንበብ
- የሚሞሉዋቸው ቅጾች ሲሰጡዋቸው
- በይፋ ሲጠየቁ

የቋንቋ ድጋፍ እንዴት እጠይቃለሁ?

ከKCSO ጋር ለመግባባት እገዛ ካስፈለግዎት ለምክትል ወይም ለማንኛውም የKCSO አባል ያሳውቁ።

እንግሊዝኛ በተወሰነ መናገር የሚችሉ ከሆነ፦

- እንዲህ ይበሉ፦ "አስተርጓሚ እፈልጋለው። የምናገረው ቋንቋ [ቋንቋዎ ያስገቡ] ነው።"

የKCSO አባል እርስዎን ከባለሙያ አስተርጓሚ ጋር ለማገናኘት Language Line ይጠቀማል።

እንግሊዝኛ ከነጭራሹ የማይናገሩ ከሆነ፦

- የKCSO አባል ቋንቋዎን ለመለየት "ወደ ቋንቋዎ ጠቁም (Point to Your Language)" የሚል ቡክሌት ወይም የሞባይል መተግበሪያ ይጠቀማል።
- የKCSO አባል እርስዎን ከባለሙያ አስተርጓሚ ጋር ለማገናኘት Language Line ይጠቀማል።

Language Line ምንድን ነው?

Language Line ማለት **አሜሪካን የምልክት ቋንቋ (American Sign Language, ASL)** ጨምሮ ከ**240 በላይ ቋንቋዎች** ብቃት ካለው አስተርጓሚ ጋር **በፍጥነት** ለማገናኘት የKCSO አባላት የሚጠቀሙበት የስልክ ወይም የቪዲዮ አገልግሎት ነው። ይህ በመረጡት ቋንቋ ከእርስዎ ጋር እንድንገናኝ ያስችለናል።

የተወሰነ እንግሊዝኛ አውቃለሁ። አስተርጓሚ የግድ ያስፈልገኛል?

አዎ።የተወሰነ እንግሊዘኛ ቢናገሩም ወይም ቢረዱም አስተርጓሚ በሚከተሉት ይረዳዎታል፦

- አለመግባባቶችን ማስወገድ
- ትክክለኛ መረጃ መስጠት
- ህጋዊ መብቶችዎን መረዳት
- እንደ የተጎጂዎች አገልግሎቶች ወይም የተተረጎሙ ቅጾች ያሉ አገልግሎቶችን መጠየቅ

አስተርጓሚ መጠየቅ ምንም ችግር የለውም?

አዎ። ሁሉም ሰው መረጃን የመረዳት እና በእጅጉ በሚመቸው ቋንቋ የመግባባት መብት አለው።

ልጄ፣ የቤተሰቤ አባል ወይም ታዛቢ ሊተረጉመልኝ ይችላሉ?

አይችልም። በKCSO ፖሊሲ እንደተገለጸው አፋጣኝ የደህንነት ስጋቶችን ከሚያካትቱ አስቸኳይ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር፣ KCSO የቤተሰብ አባላትን፣ ልጆችን ወይም ተመልካቾችን እንደ አስተርጓሚ አይጠቀምም።

አስተርጓሚ ለመጠቀም ጠቃሚ ምክር

ከአስተርጓሚ ጋር ሲገናኙ

- በቀስታ እና በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች መናገር።
- አስተርጓሚው መናገር እንዲችል ረዘም ላለ ጊዜ ዝም ማለት።
- ተራ በተራ መናገር። አንዱ እየተናገረ በማሀል አለመናገር።
- በማንኛውም ጊዜ ማብራሪያ ይጠይቁ።